ርእስ አንቀጽ

# ከአቡነ መልከጼድቅ

“ዘበአንቲሃ ለቤተ ክርስትያን ተጸፋአከ በውስተ ዓውድ” ስለ ቤተክርስትያን፤ ስለ ክርስትያኑ ሕዝብ ድኅነት በአደባባይ ተዋረድክ፡ ተገፈፍክ፤ ተገረፍክ። መድሃኔአለም የሚለው ስሙ ከዚህ ጥቅስ ጋር ይስማማል። የዓለሙ ሁሉ መድሃኒት ለመሆን ስለ ዓለም ስትል

ተደፋህ፤ ተገረፍክ፤ ተመታህ ግን ለዓለም ሁሉ ቤዛ መድሃኒትም ሆንክ።

ክርስቶስ ሰለ ቤተክርስትያን ራሱን እንድሰጥ፤ መስዋእትም፤ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ...ክርስቶስ ቤተክርስትያንን እንደወደደ ስለ እርስዋም ራሱን እንደለወጠ ያስረዳናል። (ኤፌ 5፤25) ቤተክርስትያን ክርስቶስ የሞተላት ተቓም ናት ግን እርስዋን ቤተክርስትያን የሕይወት መዝገብ አድርጉዋታል፤ ከእርስዋ ውጭ ድህነት ድኅነት እንደሌለ አድርጎ አቕቕሙትዋል።

ክርስቶስ ሕዋርያትን ጥብቅ መሰረት አድርጎ በሕዋርያት መሰረት ላይ ቤትክርስትያንን አንጹአል። “እኔም እልሃልሁ አንተ ድንጋይ ነህ በዚች ድንጋይ ላይ ቤተክርስትያን እሰራለሁ። የገሃነም ደጆች አይገለብጣትም።” ሲል ራሱ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ያስረዳል። (ማቴ 16፤18) ይህን ተከትሎ ቅዱስ ጳውሎስ የቤተክርስትያን መሰረት ጥብቅ እንደሆነ ክርስቶስ “በሃዋርያትና በነቢያት መሰረትነት እንደመሰረቱዋት በሃዋርያትና በነቢያት መሰረት ላይ ተሰርችሁ። የማእዘኑ ራስ ድንጋይ እርሱ እየሱስ ክርስቶስ ነው።” ሲል ቤተክርስትያንን ጊዜያዊ፤ ቅጽበታዊ፡ የይድረስ ስራ



አለምሆኑዋን ገልጥ ተናግሮታል። (ኢፌ 2፤20)

ይህችን ቤተክርስትያን የራሱ ምድራዊ መንግስት አድርጎ ህጉ የሚነገርበት፤ ስሙ የሚቀደስበት አድርጉዋታል። ይህችን ቤተክርስትያን አሁንም የሚጠብቅ ስለ እርስዋ የሚናገር፤ የሚሰራ መድሃኔአለም ክርስቶስ ነው። ስለዚህ እኛ ቤተክርስትያንን በተቀበልንበት መልክ መጠበቅ አለብን፤ ስለ ቤተክርስትያን ክብር፤ ስለ ቤተክርስትያን ህይወት ሲል ክርስቶስ ህማምን መከራን ተቅብሉዋልና። ስለ ቤተክርስትያን አሁንም የሚሰራ፤ የሚናገር መድሃኔዓልም ክርስቶስ ስልሆነ የቤተክርስትያንን ቅድስናዋል ሃዋርያዊ ጠባይ መጠበቅ አለበት። ክርስቶስ ራሱ የሚሆነን እኛም አካሉ የምንሆንበት ቤተክርስትያን ሆነን ተሰርተን፤ ቤተክርስትያን ሆነን ለሱ ማደርያነት በቂ ሆነን

ስንገኝ ነው። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ “እርሱም የስጋው የቤተክርስትያን ራስ፤ እርሱም መጀመርያ የሙታን በኩር እርሱ በፊት ይሆን ዘንድ በሁሉ” ሲል የክርስቶስን ራስነት፤ የእኛን አካልነት በቤተክርስትያን አማካይነት የሚገኘውን ግኑኝነት ገልጦ ያስተምራል”። (ቆልስ 1፤18) ቤተክርስትያን የሚስጥራት መዝገብ፤ የሚስጥራት ፈጻሚ ሆና በመገኘቱዋ ቤተክርስትያን አካልነቱዋ፤ ክርስቶስ ከሱዋ የማይለያት መሆኑን እንረዳለን። እንግዲህ ክርስቶስ በደሙ የመሰረታት መሆኑን ስለ ቤተክርስትያን ሲል ክርስቶስ መከራን የተቀበለላትን እኛ እንደ ዓይነ ብሌን እድርገን መጠበቅ፤ እንደ አላማዋም መፈጸም ግድ ይኖርብናል። ቤተክርስትያንን እንደ አላማዋ ካልጠበቅናት፤ ዓላማዋን ከረሳን ክርስቶስ ስለ እርሱዋ መሞቱን መከራ መቀበሉን መርሳታችን ነው። ስለዚህ የቤተክርስትያንን ዓላማ ጠንቅቀን ማወቅ እንደዓላማዋም ፈጻሚዎች ሆነን መገኘት የሁላችን ግዴታ ይሆናል። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይናገራል “አላወቃችሁምን እናንተ የእግዚአብሄር መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሄርም መቅደስ አድሮባቹሃል። ማንም የእግዚአብሄርን መቅደስ ቢያጠፋ እርሱንም እግዚአብሄር ያጠፈዋል። የእግዚዓብሄር ቤት የተቀደሰ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ። (1ኛ ቆሮ 3፡16) ራሳችን ቤተክርስትያን መሆናችንን ቅዶስ ጳውሎስ ሰፋ አድርጎ የገለጠው ራሱን ከቶ የሚጠላ የለም፤ ይማግበዋል፡ ይንከባከበዋል እንጂ፤ እንግዲያውስ የክርስቶስ ማደርያ ለመሆን የተሰራን ቤተክርስትያን መሆናችንን እንወቅ፡ እንደ ቤትክርስትያችን የክርስቶስ ማደርያ ለመሆን እንዘጋጅ። ክርስቶስ ስለ ቤተክርስትያን መከራን ተቀብሉአልና።